# የውስጥ አራዊት

ዶ/ር ኤረንካ ቀልብሰው

ስገባኝ መትጋት፥ ለጋራ መሥራት፥ በተሻለ ከወላጅ፤
ማገልገል ትቼ፥ ጀመርኩ፥ ራስ መጥቀም ወዳጅ።
ከውርስ ወይ ከአስተዳደግ፥ ያገኙኝ አራዊት፤
መናናቅ፥ ጥላቻ፥ ዘረኝነት፥ ለመጥቀስ ጥቂት።

እህት ወንድም ተርቦ እቤት፥ የሚቀመስ ጠፍቶ፤
እበልጣለሁ ማለት ከንቱ፥ አደባባይ ከባዶ ተነስቶ።
ቀረ መስማማት፥ መኖር አብሮ መትጋት፤
እንዳያጠፉኝ ፈራሁ፥ ሲጨመር ምቀኝነት።

ሥጋዬን ትተው፥ አሰቃዩት፥ አሸበሩት መንፈሴን፤
ሁሉን ላለማመን፥ እንዲቆርጥ፥ አደርጉት ነፍሴን።
ታዲያ! አንዱን ስገላገል፥ እየተተካ ሌላ፤
ልቤን አጠፋው፥ አደረገው እንዳይኖረኝ መላ።

ከውስጥ ተነገረኝ፥ ፈጽሞ ለሰው እንዳልራራ፤
የውስጤ አራዊት፥ ሁሌ አሳዩኝ መከራ።
ሳላውቀው ተውኩት፥ ማሰብ ለሌላ፤
እኔን አስቀደምኩ፥ ሌላውን ኋላ።

ጭካኔ ለምጄ፥ መኖር ጀመርኩ፥ ራሴን አብልጬ፤
ወገን ሲቸገር፥ አየሁ በዝምታ፥ ዐይኔን አፍጥጬ።
ስልጣን፥ ጥቅም፥ ሽቀጥ ሁሉ፥ አደንድኖት ልቤን፤
ከአዕምሮዬ፥ ኮበለለ ርህራሄ፥ ረስቼው ፈራሽነቴን።

ዐይኔ ታወረ፥ ይሉኝታ ጠፉ፥ ዋጠኝ ግለኝነት፤
ወንድሜን ገደልኩ፥ ለሽቀጥ፥ አቃጥሎኝ ምቀኝነት።
ማንነቴን ሳላውቅ ኖርኩ፥ በባዶ ኩራት ተነፍቼ፤
ለካስ ራቁቴን ነኝ፥ እባካችሁ! አልብሱኝ ወገኖቼ።

አብሮ መኖር፥ መሥራት ተስኖኝ፥ ለመድኩ ልመና፤
ኩራት ግብዝነት፥ ነስተውኝ ማሰላሰል፥ አስቀሩኝ መና።
የሰው ልጅ ጥላቻ፥ አንገቴን አጣሞት፤
እየለመንኩ ከምበላ፥ ይቅርብኝ ሕይወት።

ወገን ሲራብ፥ ሕፃን ሲያለቅስ፥ አለጊዜ ሲሞት፤
ሆኜ ወላጅ፥ ዘመድ፥ ሰለቸኝ ማየት፥ መስማት።
ተስፋዬ መንምኖ፥ እንዳልቀር፥ ዘርግቼ እጆች፤
አግዙኝ ወገኖች፥ ጥቃት፥ ልመና፥ እንዳይማሩ ልጆች።

ትግሌ ይቀጥላል፥ አራዊት እንዲለቁኝ፤
ለጤንነት እባካችሁ፥ መድኃኒት አፋልጉኝ።
እንዲያው ጸልዩልን፥ ለመሰሎቼ ጭምር፤
መናናቅ ለቆን፥ እንድንሠራ ቁምነገር።

For constructive feedback: ekelbisow@juno.com